# የኢትዮጵያ ሴቶች ማኒፌስቶ

# ETHIOPIAN WOMEN'S MANIFESTO



**ኢ.ሴ.ማ.ቅ**

**በኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት የታተመ**

# የኢትዮጵያ ሴቶች ሚኒፌስቶ

ግንቦት

2013

# ማውጫ


የኢትዮጵያ ሴቶች ማኒፌስቶ አዘገጃጀት ላይ የሳተፉ የሲቪል ማኅበራት 1

መግቢያ 01

የማኒፌስቶ አዘገጃጀትና ሂደት 02

የሴቶች ሁኔታ በማህበራዊ ዘርፎች እና ጥያቄዎቻቸዉ 03

ሴቶች እና ትምህርት 04

06 የሴቶች እና ጤና

08 ሴቶች እና ምጣኔ ሃብት

10 የሴቶች ውሳኔ ሰጪነትና የፖለቲካ ተሳትፎ

11 ፆታዊ ጥቃት

ሴቶች እና የመሰረተ ልማት ተደራሽነት 13

በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሴቶች 13

ሴቶች የአካባቢ ጥብቃና የአየር ንብረት ለውጥ 15

የሴቶች ጥያቄ በመልካም አስተዳድር፣ በሠላም እና ደህንነት 15

16 የሴቶችን ጥያቄ ለመመለስ ያሉ ተቋማትና አደረጃጀቶችን በሚመለከት የሴቶች ጥያቄዎች

16 በመገናኛ ብዙሀን ዙሪያ የሴቶች ጥያቄዎች

17 ሌሎች ጉዳዮች

18 ማጠቃለያ

ይህ የኢትዮጵያ ሴቶች ማኒፌስቶ ስማቸው ከታች በተዘረዘሩ የሲቪል ማኅበራት በጋራ ተዘጋጀ
ግንቦት 2013 ዓ.ም

1. የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት (ኢሴማቅ)
2. ሣራ ፍትህ ከሁሉም የሴቶች ማኅበር
3. ሴታዊት የበጎ አድራጎት ድርጅት
4. ሲቄ የሴቶች ልማት ማህበር
5. የሴቶች ይችላሉ ማኅበር
6. ፋሚሊ ሰርቪስ አሶሴሽን
7. የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሞያ ሴቶች ማኅበር
8. የኢትዮጵያ ሴቶች ሃኪሞች ማኅበር
9. ፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር
10. የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር
11. የወጣት ሴቶች ክርስቲያናዊ ማኅበር በኢትዮጵያ
12. የእራስ አገዝ ቡድኖች ህብረት /ይታወቅ ጥምረት/
13. እራስ አገዝ የሴቶች ድርጅት /ዋይዝ/
14. የሴቶች ማረፊያ እና ልማት ማኅበር
15. አዲስ አበባ ከተማ ሴቶች ማኅበር
16. የጋምቤላ ክልል ሴቶች ማኅበር
17. የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ሴቶች ማኅበር
18. አማራ ሴቶች ማኅበር
19. የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኛ ሴቶች ብሔራዊ ማኅበር
20. ቤዛ ውመንስ አሶሴሽ ኢን ኒድ
21. ቁመን የሴቶች ልማት ማኅበር
22. የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን
23. የኢትዮጵያ ወጣቶች ፌዴሬሽን
24. ኒው ሚሊኒየም ውመን ኢምፓወርመንት ኦርጋናይዜሽን
25. ጉድ ሳማሪታን አሶሴሽን
26. ምኸኸጓ ሎካ የሴቶች ልማት ማኅበር



# 1.መግቢያ

የኢትዮጵያ ሴቶች ማኒፌስቶ የተዘጋጀው በ6ተኛ አገር አቀፍ ምርጫ ተሳታፊ ሆነው ሕዝብ የማስተዳደር ኃላፊነትን የሚረከቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሴቶች የእኩልነትና የፍትህ ጥያቄዎች ላይ ሊወስዱ ያሰቧቸውን እርምጃዎች ለመመዘንና መወሰድ ያለባቸዉን እርምጃዎች ለማመላከት ነው ፡፡

ለበርካታ ጊዜያት በተለያዩ አካላት እና በሴቶች መብት ተሟጋቾች የሚነሱ ቁጥራቸው የበዛ ጥያቄዎች መኖራቸው የሚታወስ ነው፡፡ የማኒፌስቶው አስፈላጊነትም ይነሱ የነበሩ ጥያቄዎችን ጠቅለል ባለ መልኩ ለተወዳዳሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ለማሳወቅ አንደኛው ዓላማው ሲሆን፤ በምርጫ አብላጫ ድምጽ አግኝቶ የሚመረጠው ፓርቲ በሚመሰርተው መንግስት ውስጥ አንገብጋቢ የሆኑ የሴቶች ጥያቄዎችን በመገንዘብ ትኩረት እንዲሰጥና የተጀመሩ መልካም ስራዎች እንዲቀጥሉ እንዲሁም ተጨማሪ ስራዎችን ሰርተው ለጥያቄዎች ስር ነቀል ምላሽ እንዲሰጡ ለማመላከት ነው፡፡

ማፌስቶውን የማዘጋጅት ሂደቱ በነባር መረጃዎችና የተሰሩ ጥናቶችን መሰረት በማድረግ ዋና ዋና ክፍተቶች ላይ በማተኮር በመጪው ምርጫ የሚሳተፍ ፓርቲዎች እንዲያውቋቸውና ይዘው በመጧቸው ፕሮግራሞች ላይ የሴቶችን የፍትህና እኩልነት ጥያቄዎች በሚወስዷቸው እርምጃዎች እንዲያካትቱ ለማስቻል ሲሆን በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ለሚደረጉ ክርክሮች እንደ መነሻና አቅጣጫ ማመላከቻ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በተጨማሪም ይህ ማኒፌስቶ ከምርጫው በፊትም ሆነ በኋላ የግፊት ስራ (አድቮኬሲ) መገልገያ መሣሪያ እንዲሆን የተዘጋጀ ነው ፡፡

# የኢትዮጰያ ሴቶች ሁኔታ




ሴቶች ከኢትዮጲያ ከጠቅላላው የአገሪቱ የሕዝብ ብዛት ውስጥ 51 በመቶ የሚሆነውን ይሸፍናሉ፡፡ እነዚህ ሴቶች ታዲያ በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያየ የአኗኗር እና የአሰፋፈር ዘዬ ተሰባጥረው የሚገኙ ሲሆን ለምሳሌ በከተማ፣ በገጠር፣ በግብርና የሚተዳደሩ፣ በአርብቶ አደር አካባቢ ያሉ፣ በትናንሽ ከተማና በዋና ከተማ የሚኖሩ፣ በመንግስና በግል ስራ የሚተዳደሩ አሉ፡፡ሴቶችን በእድሜ ሁኔታ ሲታዩ ከህፃናት ሴት ልጆች ጀምሮ ታዳጊ ሴት ልጆች፣ ወጣት ሴቶች፣ በመውለድ እድሜ ክልል ያሉና ከዚህ እድሜ በላይ ያሉ ሴቶችን ሁሉ ያካትታል፡፡

የጠቅላላውን የአገሪቱን 51 በመቶ ማለትም ከግማሽ በላይ የሕዝብ ቁጥርን የሚሸፍኑት ሴቶች ከወንዶች አንጻር በማኅበራዊ በፖለቲካዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ተሳታፊነታቸው እና ተጠቃሚነታቸው አንጻር ሰፊ ክፍተቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ለዚህ ደግሞ በርካታ መዛግብትን እና ጥናታዊ ጽሑፎችን እንዲሁም የዳሰሳ ጥናቶችን ማጣቀስ ይቻላል፡፡

የዚህ ክፍተት መነሻም፣ በማኅበረሰብ ደረጃ ያሉ አመለካከቶች፤ ደንቦች፤የስራ ከፍፍሎች፤የትምህርትና የምጣኔ ሀብታዊ እድሎችን የማግኘት ሁኔታ፤በዉሳኔ ሰጪነት ዙሪያና ሀብት በማፍራት ሁሉ ቅድሚያ ለወንዶች መሰጠቱ እንደሆነም ዋነኛው ምክንያት ተደርጎ ይነሳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሴቶች በተለየ ሁኔታ ለጾታዊ ጥቃቶች ተጋላጭነታቸዉና ተጠቂነታቸዉ ከፍ ማለቱ ደግሞ ሌላኛው ተግዳሮት ነው፡፡

እነዚህ ሁሉ ሰዉ ሰራሽ የሆኑ ያመለካከት ክፍተቶችም በግለሰብ፤ በቤተሰብ፤በማኅበረሰብ ደረጃ የሚንጸባረቁ በመሆናቸው እና በድርጊትም ጭምር በመገለጻቸዉ ሴቶች ማግኘት የሚገባቸዉን ጥቅሞች እንዳያገኙ እንቅፋት ሆነው ቆይተዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን የሴቶች ችግሮችን ለመፍታት መንግስትና የሲቪል ማኅበራት ብዙ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ ከነዚህም የግንዛቤ ማስጨበጫ፤የህግ ማሻሻያዎች፤ የመዋቅር ለውጦች፥ የሴቶችን ኢኮኖሚ አቅም የሚያሳድጉ እድሎችን መክፈት፥ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ማሻሻል እንዲሁም ለሴቶች የትምህርትና ስራ እድል እንዲያገኙ አዎንታዊ ድጋፎችና የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል። እነዚህ ጥረቶችም ለዉጦች ያመጡ ቢሆንም አጥጋቢ እና አመርቂ በሚባል ደረጃ ባለመሆኑ አሁንም ብዙ እርምጃዎችንና ውሳኔዎችን መዉሰድ ይጠይቃል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃም ባሉ የስርአተ ፆታ እኩልነት መለኪያ መስፈርቶች አንዱ በሆነዉ Global Gender Gap Index መሰረት ኢትዮጲያ ከ153 አገሮች 82ኛ ላይ ትገኛለች፡፡ ይህ መለኪያ አገራትን በትምህርት፤በጤና፤በፖለቲካና በምጣኔ ሀብት ተሳትፎ ሴቶች ያሉበትን ደረጃ ያወዳድራል፡፡ (world Economic Forum 2020) በሌላ በኩል Gender Inequality Index ልኬት በሶስት መልኮች /አቅጣጫዎች አገራት የሚያወጡትን የልማት ስኬት የሚሰድር ሲሆን፤ እነሱም የተዋልዶ ጤና፣ ሴቶችን የማብቃት ሁኔታ፣ እና የስራ ተሳትፎን ያጠቃልላል፡፡ በዚህ ልኬት መሰረትም ኢትዮጵያ ከ 160 አገራት 121ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የኢትዮጵያ ሴቶች ሁኔታን ለማሻሻል ብዙ ጥረቶች እየተደረጉ ቢሆንም ከችግሮቹ ስፋትና ጥልቀት አንጻር ብዙ ስራዎች ይቀራሉ፡፡ ይህ የኢትዮጵያ ሴቶች ማኒፌስቶም የቀሩ ስራዎችን፣ እንዲሁም እስካሁን ትኩረት ያላገኙ የሴቶች ጥያቄዎችን ያቀርባል፤ አቅርቦም መፍትሔ እንዲያገኙ በማድረግ በኩል ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

# 2.የማኒፌስቶ አዘገጃጀትና ሂደት

ይህ ማኒፌስቶ የተዘጋጀው በኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት፤ በስሩ ባሉ 29 መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሲቪል ማኅበራት እንዲሁም የሴቶች ጉዳዮች የሚሰሩ ሌሎች ሲቪል ማህበራት ነው፡፡ የአዘገጃጀት ሂደቱም በ1997 ዓ.ም ለተደረገዉ 3ተኛዉ ሀገራዊ ምርጫ በኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር፣ በኢሴማቅ እና አጋሮቻቸው ተዘጋጅቶ የነበረዉን የሴቶች ማኒፌስቶ መነሻ አድርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ አገራት የተዘጋጁ ማኒፌስቶዎችን በመመልከትም ልምድ ተቀስሞበት የተዘጋጀ ሲሆን የኢሴማቅና አጋሮቹ በተለያዩ ወቅቶች በሴቶች አጀንዳዎች ላይ ባደረጉዋቸው ውይይቶች ላይ የሲቪል ማኅበራት እና ስርዓተ ጾታ ባለሙያዎች ካጠኗቸው ጥናቶች ፥ እንዲሁም ለመንግስት ባቀረቡዋቸው ማመልከቻዎች የተካተቱትን ነጥቦች መሰረት አድርጓል። በመጀመሪያው የዚህ ማኒፌስቶ ረቂቅ ከክልልና ከአዲስ አበባ የተገኙ የሴቶች ማህበራትና ግብዓት ተገኝቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከመንግስት በኩል የሚወጡ መረጃዎችንም በመመርኮዝ የሴቶችን ዘርፈ ብዙ ጥያቄዎች በየደረጃው ለማጠናከር እና ለማካተት ጥረት ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም ሰነዱ በኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት አዘጋጅነት የስርአተ ፆታ ባለሙያዎችና የተለያዩ አገር በቀልና ዓለም አቀፍ ሲቪል ማኅበራት ጋር በየሳምንቱ በበይነ መረብ በሚደረገው ዉይይት መድረክ ላይ ቀርቦ እንዲዳብር ተደርጓል። የተሰጡ ግብአቶችም በዚህ ማኒፌስቶ ላይ ተካተዋል፡፡ ይህ ሰነድ በእነዚህ ሂደቶች አልፎ ተሰናድቷል።

# 3. የሴቶችና የማኅበራዊ ዘርፍ ጥያቄዎቻቸው



# 3.1 የሴቶች ሁኔታ በትምህርት

ትምህርት ለሁለንተናዊ እድገት መሰረት መሆኑ እሙን ነው፡፡ ይሁን እንጂ በኢትዮጲያ ውስጥ ያለው የትምህርት ተደራሽነት ግን በወንድ እና ሴት ጾታ መካከል ልዩነቶች በጉልህ የሚታይበት ነው፡፡ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ከፈረመቻቸው ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶች መካከል የትምህርት ዕድል ተደራሽነት ለሁሉም መዳረስ የሚደግፍ ቢሆንም ነገር ግን አሁንም በሙልአት አልተፈፀመም። ለዚህም አንዱ ማሳያ የሚሆነው ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ ያለው የሁለቱም ፆታዎች እኩል ተሳትፎ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ሲደርስ የሴቶች ቁጥር ማነሱ ነው።

ለዚህም ዋና ዋና ምክንያቶች

*የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከመኖሪያ አካባቢዎች መራቅ
*ሴት ልጆች ለጥቃት ይጋለጣሉ ይዳረጋሉ በማለት የቤተሰብ ስጋትና ይህንንም ተከትሎ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አለመላክ
*በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚፈፀሙ ፆታዊ ትንኮሳዎች
*ያለእድሜ ጋብቻ
*ሴት ልጆችን ወደ ትምህርት ቤት ከመላክ ይልቅ በቤት ውስጥ ባሉ ስራዎች እንዲያግዙ መፈለግ
*ሴቶች በጥናት የሚያሳልፉት ሰዓት ከወንዶች ይልቅ አናሳ መሆን
*የጥናት ሰዓታቸው በቂ ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ ውጤታቸው ዝቅ ማለት

ከላይ የተጠቀሱትን ምክንያቶች እና ተግዳሮቶች በማለፍ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገቡ ሴቶች ከወንዶች አንጻር ቁጥራቸው ከቀዳሚዎቹ ዓመታት አንጻር ሲተያይ ጭማሪ ቢያሳይም አሁንም ግን አጥጋቢ አይደለም፡፡ ይህም ደግሞ በቀጣይ ሰፊ ስራዎች እንደሚያስፈልጉት ማሳያ ነው፡፡
ሴት ልጆች በትምህርት ቤት ውስጥ በርካታ ችግሮች ያጋጥማቸዋል፡፡ ከሰው ሰራሽ ችግሮች ባለፈም ከተፈጥሮ ጋር በተያያዘ በወር አበባ ወቅት በቂ እውቀትና ግንዛቤ ስለሌላቸውና የንፅህና መጠበቂያ በበቂ ሁኔታ ስለማያገኙ ከትምህርት ቤት እንዲቀሩ ይገደዳሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ወደ ትምህርት ቤት ቢሄዱ እንኳን የመሸማቀቅና በተለያዩ የስነልቦና ጫና ውስጥ ሆነው ቀናቸውን ያሳልፋሉ፡፡
በገጠር አካባቢዎች ሴት ልጆች በአማካኝ በወር ውስጥ ከ 4-5 ቀን ከትምህርት ቤት ይቀራሉ፡፡ ይህ ከትምህርት ገበታ የመቅረት ሁኔታም ዘመናዊ የወር አበባ ንፅህናን በማይጠቀሙት ሴት ልጆች ላይ ከፍ ብሎ ይስተዋላል፡፡ ዘመናዊ የወር ንጽህና መጠበቂያ በዋጋ ደረጃ ከ 25-45 ብር ሲሆን መንግስት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ላይ ተጥሎ የነበረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ከ 30% ወደ 10% ዝቅ እንዲል ውሳኔ ማስተላለፉ ይታወሳል፡፡ እንዲሁም በአገር ውስጥ ለሚያመርቱ ደግሞ ጥሬ እቃው ከቀረጥ ነፃ እንዲገባ ተፈቅዷል፡፡ ይህ ጥሩ እርምጃ ቢሆንም ወደ በተግባር ላይ በማዋል ሂደቱ ላይ ግን አሁንም ችግሮች ተቀርፈዋል ለማለት አያስደፍርም፡፡

በሌላ በኩል ከሰው ሰራሽ የሴቶች ተግዳሮት ውስጥ አንደኛው እና ዋነኛው ጾታዊ ጥቃት ሲሆን ይህም ሌላው ሴት ልጆች በትምህርት ቤት አካባቢ የሚያጋጥማቸው እና ከትምህርት ገበታ እንዲሰናከሉ የሚያደረጉበት ትልቁ ችግር ነው፡፡ ከሚደርሱባቸው ጥቃቶች ውስጥ እንደ ማሰፈራራት ፣ መከታተል፣ማስጨነቅ፤ ድብደባ የመሳሰሉ የወሲባዊ ትንኮሳ አስገድዶ መድፈር እና ሌሎች ተጨማሪ ፆታዊ ጥቃቶች የመጋለጥ ዕድላቸው እጅግ የጨመረ ነው፡፡ በሚደርስባቸው ጥቃትም ትምህርት ማቋረጥ ፣አካባቢ ጥሎ መጥፋት ወይም መሰደድ፣ በጣም ሲብስም እራስን እስከማጥፋት የሚደርሱ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፡፡ በተለይ በከተሞች አካባቢ በትምህርት ቤቶች ዙሪያ የሚከፈቱ የአልኮል መጠጦች መሸጫ እና ጫት ቤቶች ተማሪዎችን ለተለያዩ ሱሶች በመዳረግና የሴት ተማሪዎች ጾታዊ ጥቃት እንዲደርስባቸው ተጨማሪ ምክንያት በመሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረጉ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ፡

በዩኒቨርስቲዎች አካባቢ በተሻለ ሁኔታ የስርአት ፆታ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተሻለ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተለይም በመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የስርአት ፆታ ቢሮዎች ተቋቁመው በስራ ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ቢሮዎች በተለይም በዩኒቨርስቲ ውስጥ ያሉ የሴት ተማሪዎችን ችግሮች በመለየት ልዩ እገዛ የሚያስፈልጋቸዉን ሴት ተማሪዎች የተለያየ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋሉ፡፡ ለምሳሌ ከዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የመጡ ሴት ተማሪዎችን የገንዘብና ቁሳቁስ እንዲሁም የንፅህና መጠበቂያዎችን እንዲያገኙ እድሎችን ያመቻቻሉ ፡፡ በተጨማሪም ለሴት ተማሪዎች የልዩ የትምህርት ዕገዛ /የጥናት ፕሮግራሞችን፣ የቋንቋ እና የኮምፒውተር ስልጠናዎችን/ ከትምህር [illegible] ጋር በመተባበር እንዲያገኙ ያደርጋሉ፡፡ ይሁን እንጂ ደ[illegible]ም ዩኒቨርስቲዎች ዉስጥ ተደራሽ ሲሆን ወይም ሲተገ[illegible]፡

# በትምህርት ዙሪያ የሴቶች ጥያቄዎች

1. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከመኖሪያ አካባቢያቸው በቅርብ ርቀት ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ

2. ማኅበረሰቡ ሴትን ልጅ ማስተማር ያለውን ጉልህ ጠቀሜታ በውል እንዲገነዘብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ቅስቀሳዎች እና ስራዎችን ማካሄድ

3 ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ካላቸዉ ቤተሰቦች የመጡ በየደረጃዉ ያሉ ሴት ተማሪዎችን በትምህርት መሳሪያዎችና ለንፅህና መጠበቂያ በሚያስፈልጉ ወጪዎች መደገፍ እና ይህም በመንግስት በጀት ውስጥ እንዲካተት

4. ትምህርት ቤቶች ለሴት ተማሪዎች በተለይ ደግሞ ለአካል ጉዳተኛ ሴት ተማሪዎች ምቹ እንዲሆኑ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡



5 በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ መጸዳጃ ቤቶች ለአካል ጉዳተኛ ሴት ተማሪዎችና በአጠቃላይ ለሴት ተማሪዎች ምቹና ተደራሽ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

6. የሴት ልጅ ጥቃትን የማይቀበል እና በቸልታ የማያልፍ ትምህርት ቤትና አካባቢን በመፍጠር በትምህርት ቤቶች አካባቢ የሚፈጸሙ ፆታዊ ጥቃቶችን ለመከላከል አስገዳጅ የሆነ መመሪያ መዉጣት አለበት፡፡

7. የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራም በሁሉም ክልሎች እንዲስፋፋ መደረግ አለበት፡፡

8. በአጠቃላይ የትምህርት መሳሪያ አቅርቦት እጥረት ሴት ልጆችን በበለጠ የሚጎዳ በመሆኑ በተለይ በገጠር እና በታዳጊ ክልሎች በቂ የትምህርት መሳሪያ አቅርቦትና እገዛ ሊኖር ይገባል።

9 ትምህርት ቤቶችን ለሴት ተማሪዎች እና ለአካል ጉዳቶኞች ምቹ ለማድረግ ለሚሰሩ ስራዎች መንግስት በቂ በጀት መመደብ ይኖርበታል፡፡

10 .ሴቶች በቤት ውስጥ የሚያጋጥማቸውን የስራ ጫና የሚቀንስበት እና የሚቃለልበት መፍትሄ ሊበጅ ይገባል፡፡

11 ሴት ልጆች በቂ የትምህርት ዝግጅት እንዲኖራቸው የሚያስችል ልዩ የትምህርት ዕገዛ እንዲያገኙ የቴክኖሎጂ ተደራሽነትን ማስፋት እና በተለይም የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ

12 በሴት ተማሪዎች በብዛት ሲደፈሩ የማይታዩትን የሳይንስና ቴክኖሎጂ የትምህርት ዘርፎች ሴቶች እንዲመርጧቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡

13 በትምህርት ቤት ውስጥ ሴትና ወንድ ተማሪዎች እድሜያቸውን የሚመጥን የስነ ተዋልዶ ጤና ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ

14 የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች አካታች በሆነ መንገድ አስፈላጊውን አጋዥ የትምህርት መርጃ መሳሪያ በመጠቀም ጥራት ያለው ያለው ትምህርት እንዲያገኙ መደረግ ይኖርበታል፡፡

15 መምህራንን በስርአተ ጾታ ጉዳዩች ዙሪያ ግንዛቤያቸው እና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው በስርዓተ ጾታ የተቃኘ እና ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

16 መደበኛ ትምህርት ያላገኙ ሴቶች በተግባር ተኮር የጎልማሶች የትምህርት መርሀ ግብር መሰረት እንዲማሩ መመቻቸት አለበት፡፡ በተለይም በአበባ እርሻዎችና በኢንዱስትሪ መንደሮች አካባቢ ለሚሰሩ ሴቶች ትኩረት መደረግ አለበት፡፡



# 3.2 ሴቶች እና ጤና






ሴቶችና ወንዶች ተፈጥሯዊ በሆነ ምክንያት የተለያዩ የጤና ፍላጎቶችና ጥያቄዎች አሏቸው፡፡ ከዚህም ውስጥ በዋናት ደግሞ የስነ ተዋልዶ ጤና እንክብካቤ አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ ይህን ማሟላት አንዱ የመንግስት ተቀዳሚ ተግባር ሲሆን፡፤ እስካሁንም ብዙ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይቷል ፡፡ ነገር ግን አሁንም ሴቶች ከወሊድ ጋር በተያያዘ በቀላሉ ሕይወታቸውን መታደግ በሚቻልባቸው አጋጣሚዎች ለህልፈት ይዳረጋሉ፡፡ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶችም አገልግሎቱን ለሚፈልጉ ሁሉ ተደራሽ አይደለም፡፡ በተጨማሪም የታዳጊ ሴት ልጆች ካለእድሜ የማርገዝና የመውለድ ሁኔታ ከፍ ብሎ ይታያል፡፡

በአለም የጤና ድርጅት እንዳስቀመጠው የሰዎች ጤና ዕክል ተብለው ከተቀመጡ በሽታዎች ውስጥ ስርዓተ ጾታን መሰረት አድርገው የሚከሰቱ እና ተያያዥ ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ ወንዶችና ሴቶች በስርአተ ፆታ ምክንያት ማኅበረሰቡ ውስጥ ባሉ ማኅበራዊ እሴቶችና ደንቦችን ለማክበር በሚያደርጓቸዉ ድርጊቶችና በሚያሳዩዋቸዉ ባህርያት ምክንያት ጤናቸዉን ለአደጋ ሲያጋልጡ ይታያል፡፡

በተፈጥሮም ቢሆን ሴቶች ከወሊድ ጋር በተያያዘ የተለየ የጤና ፍላጎት አላቸው፡፡ በ2010 ዓ.ም የተደረገዉ የኢትዮጵያ የስነህዝብና ጤና ዳሰሳ ጥናት እንደሚያሳየው 62 በመቶ የሚሆኑ እናቶች የቅድመ ወሊድ ክትትል 32 በመቶ የሚሆኑት እስከ አራት ጊዜ የቅድመ ወሊድ ክትትል በማድረግ 26% የሚሆኑ በጤና ባለሙያ በመታገዝ የወለዱ ሲሆን 17% የሚሆኑት የድህረ ወሊድ ክትትል አድረገዋል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የእናቶች ሞት ከፍተኛ የሚባል ሲሆን ይህም በአሀዝ ሲሰላ ከ1 መቶ ሺሕ እናቶች 412 እናቶች (412/100000) ከወሊድ ጋር በተያያዘ ለሕልፈት ይዳረጋሉ ማለት ነው፡፡ የእናቶችን ሞት ለመቀነስ የተለያዩ ከፍተኛ ጥረቶች እየተደረጉ ያሉ ሲሆን ለምሳሌ ጤና ተቋማትን በማስፋፋት፣ጤና ኤክስቴንሽኖችን በማሰማራት፤የጤና ተቋማት ለወላዶች ምቹ እንዲሆኑ ለማድረግ ጥረቶች እየቀጠሉ ቢሆንም በተለይም በገጠር አካባቢዎችና በተለያዩ ሰዉ ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች በተከሰቱባቸዉ አካባቢዎች የእናቶች ጤና ሁኔታ አሳሳቢ ሆኖ ይታያል፡፡

ከተዋልዶ ጤና ባሻገር ሴቶችን በዋናት የሚያጠቁ ልዩ ልዩ የጤና እክሎች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ እንደ ጡትና የማህፀን ጫፍ ካንሰር በሀገራችን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ተስፋፍተው ይገኛሉ ፡፡ ፊስቱላና የማህፀን መውጣት አይነት የጤና ችግሮች ደግሞ ውስብስብ እና ከፍተኛ የሕክምና ወጪ የሚጠይቁ ሲሆኑ፤ ትኩረት እየተሰጣቸው ቢመጣም ትኩረቱ በቂ አይደለም።

ባለፉት አመታት የጤና አገልግሎቶች ሴቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ ከተሰሩ አዎንታዊ ተግባራት መካከል የእናቶችና ህፃናት የጤና አገልግሎት ከክፍያ ነፃ መደረጋቸውና የአንቡላንስ አገልግሎት መቅረቡ ነው፡፡ ሆኖም ከጤና ተቋማት ራቅ ካሉ ስፍራዎች በአንቡላንስ የመጡ እናቶች ከወለዱ በኋላ ወደ ቤታቸዉ ለመመለስ የአንቡላንስ አገልግሎትን ማግኘት አለመቻላቸዉ ቅሬታን ፈጥሯል። ከዚህም በተጨማሪ በገንዘብ ማጣት ምክንያት የሚፈጠረውን የህክምና አገልግሎት ችግር ለመቅረፍ በቅርቡ የተጀመረው የጤና መድን አገልግሎት የተሳካ ሙከራ ትግበራ አልቆ ወደ ማስፋፋት ተሸጋግሯል ፡፡

ሴቶች በየጊዜው ለሚከሰቱ ወረርሽኞችም ተጋላጭ የሆኑባቸው ሁኔታዎች ይታያሉ። ለምሳሌ ኮሌራ፣ወባ ኮቪድ-19 የመሳሰሉት ወረርሽኞች በስርአተ ፆታ መነፅር ሲታዩ ሴቶች በበሽታውም ሆነ በሽታው በሚያስከትላቸው የኑሮ ሁኔታዎች የበለጠ ተጋላጭና ተጎጂ ያደርጋቸዋል፡፡

# በጤና ዙሪያ የሴቶች ጥያቄዎች

- የጤና ተቋማት በእናቶችና ህፃናት ጤና ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡
- በቂ ትኩረት ያልተሰጣቸውና ሴቶችን በስፋት እያጠቁ የሚገኙ በሽታዎች ማለትም እንደ ፊስቱላ፣ የማህፀን መውጣት፣ ካንሰር እና የመሳሰሉት ችግሮችን በተመለከተ አገልግሎቶች ከክፍያ ነፃ መቅረብ አለባቸዉ፡፡ በተጨማሪም እነዚህን አገልግሎቶች ለማግኘት በሴቶች ላይ የሚደርሱ እንግልቶች መቆም አለባቸው፡፡
- ሴቶች ካሉባቸው ድርብርብ የስራ ጫና አንፃር የጤና ትምህርቶች ለነሱ በሚያመቻቸው ሰአትና ቦታ መስጠት አለባቸው፡፡
- የጤና መድን በሁሉም የገጠርና የከተማ የቀበሌዎች መጀመር አለበት፡፡
- የመድህኒት አቅርቦትና ወደ ታካሚዎች በተለይም ደግሞ ሴቶች ለተጨማሪ የሕክምና ዕርዳታ ወደ ከፍተኛ የሕክምና ተቋም የሚዘዋወሩበት አሰራርም ሊሻሻል ይገባል፡፡
- የተዋለዶ ጤና አገልግሎት በጤና ተቋሞች ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ለሴቶች የሚቀርቡ ቦታዎች ተደራሽ መሆን አለባቸው
- በወረርሽኝ መልክ የሚከስቱ በሽታዎች ለመቆጣጠርና ምላሽ ለመስጠት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በስርአተ ፆታ እይታ ተቃኝተዉ የሴቶችን ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚተገበሩ ሊሆኑ ይገባል፡፡
- ለሴቶች ጤና የሚሰጠው ትኩረት ከስነ ተዋልዶ ባለፈ የሴቶችን ልዩ ፍላጎቶች በተለይም ከአእምሮ ጤና፥ ከቀዶ ጥገና፥ ከካንሰር ህክምናና ሌሎች ተመሳሳይ የጤና እክሎችን ምላሽ ለመስጠት የሴቶችን የተለየ አካላዊና ተፈጥሯዊ ፍላጎቶች በሁሉም ደረጃ ባሉ የጤና አገልግሎቶች ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።
- በጤና ዘርፍ የፆታዊ ጥቃት መከላከልና ምላሽ የመስጠት ስራ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራና ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡
- ተፈናቃዮች ባሉባቸዉ አካባቢዎች የጤና አገልግሎቶች በተለይም ያለተፈለገ እርግዝናን መከላከል፣ ነፍሰጡር እናቶችን ክትትልና በሰለጠነ ባለሙያ ታግዘዉ እንዲወልዱ ልዩ ትኩረት መሰጠት አለበት፡፡
- በጤናዉ ዘርፍ ከስነ-ምግብ አንፃር የሚሰሩ ስራዎች ለነፍሰጡርና የሚያጠቡ እናቶች ልዩ ትኩረት መስጠት አለባቸው፡፡
- የጤና አገልግሎት ሰጪ አካላት ለሴት ታካሚዎችና ሴት የጤና ባለሙያዎችን አስመልክቶ የራሳቸው የወሲባዊ ትንኮሳ መከላከል ፖሊስ ሊኖራቸው ይገባል።
- የአእምሮ ጤናን በተመለከተ የሴቶችን የኑሮ ጫና እና የአኗኗር ሁኔታን ታሳቢ ያደረገ እንዲሁም በሰላም እጦት ለሚከሰቱ የአእምሮ ጤና ችግሮች ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡
- ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸዉ የተሟላ አገልግሎት የሚሰጡ የአንድ መስኮት አገልግሎት መስጫ ተቋማት መስፋፋት አለባቸዉ
- መሰረተ ልማት ላይ ያለውን ችግር በመቅረፍ በተለይም በውሃ እና መብራት በኩል ያለውን የአገልግሎት እና ተደራሽነት ችግር በመቅረፍ እናቶች ተገቢና በቂ እርዳታ አግኝተው በጤና ተቋም እንዲገለገሉ መደረግ አለበት፡፡
- የስነ ተዋልዶ ጤና መረጃ እና ግንዛቤ የማስጨበጥ አሰራር ለጎዳና ተዳዳሪዎች፣ ከመደበኛ ትምህርት ስርዓት ውጪ ላሉ ሴቶች፣ በአበባ እርሻ እና ኢንዱስትሪ መንደሮች አካባቢ ለሚሰሩ ሴቶች ተደራሽ መደረግ አለበት፡፡
- ከስነ-ተልዋዶ አንፃር ለሴቶች ጤና በጣም አስፈላጊ የሆኑ መድሃኒቶች በሀገሪቱ የመድሃኒት ስርዓት ውስጥ ተካተው መቅረብ አለባቸው፡፡
- በሴቶች ጤና፣ በተለይ በወሊድ እና ሌሎች የጤና ጉዳዮች ላይ በተቋም እና በግለሰብ ደርጃ ለሚፈፀሙ ግድፈቶች አግብባ ያለው የተጠያቂነት ሥርዓት መዘርጋት አለበት።

# 4. ሴቶች እና ምጣኔ ሀብት

የኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች 85በመቶ በሚሆነው በገጠራማው አካባቢ በሚተገበረው የግብርና እንቅስቃሴ ነው፡፡ በግብርና እና በአርብቶ አደርነት የኑሮ ዜየ የሴቶችንም ሆነ የወንዶችን ተሳትፎ የሚፈልግ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ የሴቶች ተሳታፊነት በተጠቃሚነት ደረጃ የተሳታፊነታቸውን ያህል ሳይሆን ከውጤቱ ዕኩል ተቋዳሽ አይደሉም፡፡

አምራቹ የሕብረተሰብ ክፍል ወደ 47በመቶ የሚሆነው በሴቶች ይወከላል፡፡ በተለይም ደግሞ በኢትዮጵያ አሁንም ዋና የአገሪቱ የጀርባ አጥንት ነው የሚባልለት ግብርና ዘርፍ ውስጥም 41በመቶ የሚሆነው ሴቶች በሚያወጡት ጉልበት የሚከናወን ነው፡፡

የተለያዩ መረጃዎች እንደሚያሳዩት መሬት በጣም ወሳኝ የምጣኔ ሀብት መሰረት ነው፡፡ በቅርብ አመታት በተደረጉ ጥረቶች የመሬት እኩል ተጠቃሚነት በተሻለ ሁኔታ እየተረጋገጠ ቢመጣም አሁንም ሙሉ በሙሉ አልተከናወነም፣ ለዚህም ማሳያ የሚሆኑት እስካሁን የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት ከሚገባቸው ሴቶች ውስጥ ያገኙት 40በመቶ የሚሆኑት ብቻ ናቸው፡፡

በመደበኛ የመንግስትና የግል የስራ ዘርፍ የመሰማራት ሁኔታን በሚመለከትም የሴቶች በከተሞች አካባቢ የስራ አጥነት ስብጥር ሲታይ 12.2 በመቶ የሚሆኑት ወንዶች ሲሆኑ፤ 26.1 በመቶ ሴቶች ሆነው እናገኛለን፡፡ በአጠቃላይም የወጣቶች የስራ አጥነት ምጣኔ በሴቶች ላይ ከፍ ብሎ ይታያል በአሀዝ ሲሰላም 18.8 በመቶ ወንዶች ሲሆኑ 31.7 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡



በተጨማሪም በምጣኔ ሀብት ዙሪያ ስራ አጥነትን በመቅረፍ በኩል እየተከፈቱ ባሉ የኢንዱስትሪ መንደሮች ለብዙ ወጣት ሴቶች የስራ እድሎች እየተከፈቱ ቢሆንም የሚያገኙት ክፍያ በጣም ዝቅተኛ መሆን (1500-3,000ብር የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችን ጨምሮ) አሁንም በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዳይችሉ አድርጓል፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚሰሩ ወጣት ሴቶች የመኖሪያ የቤት ችግር፣ የኑሮ ውድነት፣ እንዲሁም የተለያዩ ችግሮች ያጋጥማቸዋል ፡፡

ሴቶች እራሳቸውን በኑሮ ለመደገፍ እና ለመቻል ከሚያደርጓቸው ጥረቶች አንዱ ወደተለያዩ የአረብ አገራት በህገወጥ መንገድ መሰደድና በዚሁ ሁኔታዎች ውስጥ ለተለያዩ የስራ ጫናዎች፣እንግልት፣ አካል መጉደል፣ እንዲሁም ለሞት መዳረግ ነው ፡፡ የሰራተኛ እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ባወጣው መረጃ መሰረት በአመት ቁጥራቸው በርከት ያሉ ዜጎች በህገ ወጥ መንገድ ይሰደዳሉ ከዚህም ውስጥ አብዛኞቹ ሴቶች ናቸዉ ፡፡

ሴቶችን በምጣኔ ሀብት ለማብቃት በአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ለመመስረት የሚያስችላቸውን በርካታ ድጋፎች መንግስት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በፋይናንስ ስልጠና፣ የማምረቻ ቦታ በማፈላለግና በመስጠት እገዛዎች ሲደረጉ የቆየ ቢሆንም በዚህ ዘርፍ ከተከፈቱት የስራ እድሎች ሴቶች ያገኙት 41 በመቶ ብቻ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም አዲስ ስራ ለመጀመር የብድር አገልግሎት በማግኘትም ረገድ 33 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ብቻ የብድር አገልግሎት ሲያገኙ በገበያ ትስስር ከተፈጠሩ እድሎች 39 በመቶ ሴቶች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በአጠቃላይ በኢትዮጳያ ውስጥ ባለፉት 5 አመታት በአምራች ዘርፍ ፤ከተማ ገብርና ፤በግንባታ፣ በአገልግሎትና ንግድ ዘርፍ ከተፈጠሩት 3.9 ሚሊየን የስራ እድሎች 1.9 ሚሊየን (48.7%) የሚሆኑ ለሴቶች የነበረ ቢሆንም ፤ በአምራች ዘርፍ ከተፈጠሩት ተቋሞች ውስጥ 10 በመቶ የሚሆነው የስራ ዕድል ብቻ ነው በሴቶች የተያዘው፡፡ በአጠቃላይ በምጣኔ ሀብቱ ዘርፍ አመርቂ ውጤቶች ቢታዩም ሴቶችን በሁሉም ዘርፍ ተጠቃሚ ከማድረግ አኳያ የሚቀሩ ክፍተቶች አሉ፡፡







በተጨማሪም ከትላልቅ የብድር አቅርቦቶች ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶች በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ እንዲሁም የተፈጠሩ የስራ እድሎች ብዙ ሴቶችን ተጠቃሚ ያደረጉ የሚመስሉ የስራ ዘርፎችም ጊዜያዊ ናቸው፡፡

በመደበኛ ቅጥር ወቅት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 35(8) ሴቶች የቅጥር የስራ እድገት የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ መብት እንዳላቸው ይደነግጋል ፡፡ የዚህን ድንጋጌ ተፈፃሚነት ለማረጋገጥም ብዙ ጥረቶች እየተደረግ ቢሆንም የዚህ አንቀጽ ሙሉ በሙሉ ትግበራ ብዙ ተግዳሮቶች አሉት ፡፡

በአስሪና ስራተኛ አዋጅ ዙሪያም የሴቶች የወሊድ ፍቃድ ጊዜ እንዲሁም ተቋማት የህጻናት ማቆያ ስፍራዎችን እንዲከፍቱ የተላለፈው አዋጅ አበረታች ሆኖ ሳለ የአዋጁ ተፈጻሚነት ሲመዘን አሁንም ብዙ የሚቀረውና ሊፈተሽ የሚገባ ነው፡ ፡በተለይም የህጻናት ማቆያዎች ጋር ተያይዞ ገና ብዙ ተቋማት ያልተገበሩት ነገር ሲሆን፤ በተለያዩ ፋብሪካዎችና የግል ተቋማት አካባቢ ላይ ይባስ ብሎ የወሊድ ፍቃድን እንኳ በአግባቡ ለመስጠት አንዳንድ ተግዳሮቶች ይታያሉ፡፡

ሴቶች ለአገር ምጣኔ ሀብት ከሚያደርጉት ዋነኛ አስተዋጽኦ መካከል ክፍያ የማይጠየቅባቸው የቤት ውስጥ ስራዎች ለምሳሌ ምግብ ማብሰል፣ የማገዶ እንጨት መልቀም ፣ውሃ ማምጣት ፣ልጆችንና አረጋውያንን መንከባከብ የመሳሰሉት እንደ ዋና ምጣኔ ሀብት መሰረት ሆነው አይታዩም፡፡ ነገር ግን እነዚህ ስራዎች ምንም እንኳን የአምራች ኃይሉ በህይወት እንዲቀጥል ምርታማ እንዲሆን እለት ተእለት መሠራት ያለባቸው ቢሆንም በዋነኛንት እነዚህ የስራ ዘርፎች ለምጣኔ ሀብት ያላቸው አስተዋፅኦ በአግባቡ አለመሰላቱ ሌላው ችግር ነው፡፡

በኢ-መደበኛ የምጣኔ ሀብት ዘርፍም ከወንዶች ይልቅ ብዙ ሴቶች ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡ ዘርፎቹም የጉሊት ንግድ፤ ችርቻሮ ንግድ፤አቅርቦት ላይ የተሰማሩ ስራዎችና የመሳሰሉት ሲሆኑ፤ከዚህ ዘርፍም ሴቶች ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው ለእለት ጉርስ የሚሆን ያሟላሉ፡፡

# በ ኢኮኖሚ ዙሪያ ሴቶች ጥያቄዎች

- ሴቶች በዋነኛነት የሚሰሩዋቸው ክፍያ የማይከፈልባቸው የቤት ዉስጥ ስራዎች በምጣኔ ሀብት ውስጥ ያለውን አስተዋፅዖ በአግባቡ በመገንዘብ አስፈላጊዉን እውቅና መስጠት እና እነዚህን ስራዎች የሚያቀሉ የመሰረተ ልማት አውታሮች መዘርጋት ይኖርባቸዋል፡፡
- በመደበኛ የስራ ዘርፍ ተሰማርተዉ ለሚገኙ ሴቶች የህፃናት ማቆያ ስፍራዎች በሁሉም ተቋማት ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡፡
- በኢንዱስትሪ ፓርኮች ለሚሰሩ በአብዛኛዎቹ ሴቶች የመኖሪያ ቤት፤የተሻለ ክፍያ፤የትምህርትና ስልጠና እድሎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡
- በግብርና ሙያ ለሚተዳደሩ በሴት የሚመሩ ቤተሰቦች ልዩ ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡
- ሴቶችን የመሬት ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣውን ፖሊሲ በማስፈጸም የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አሰጣጥ ሒደት በተሟላ መንገድ ስራ ላይ ማዋል አለበት፡፡
- በኢመደበኛ የምጣኔ ሀብት ዘርፍ የተሰማሩ ሴቶችን ለማገዝ በፍላጎትና ክህሎት ላይ የተመሰረተ የብድር አቅርቦት፤የመነሻ ካፒታል፤የንግድ ክህሎት ስልጠናዎች፤ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡
- በኢመደበኛ፣ በተለይም በግንባታ ስራ ላይ የተሰማሩ ሴቶች ከወንዶች ያነሰ ክፍያ የሚከፈላቸው በመሆኑ፣ ይህ ደግሞ ኢ-ፍትሃዊ እና ሰብዓዊ መብትን የሚጥስ ስለሆነ የሴቶች እኩል ተከፋይነት በህግ እና በተግባራዊ እርምጃ መረጋገጥ አለበት።
- በኢመደበኛ የምጣኔ ሀብት ዘርፍ የተሰማሩ ሴቶች ህጋዊ እውቅናና የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ መደረግ አለበት፡፡
- የሴቶች ራስ አገዝ ቡድኖች አድገውና ተጠናክረው ወደ የህብረት ስራ ማኅበር ለማደግ የሚያደርጓቸውን ጥረቶች በህግ አግባብ መደገፍ፡፡
- በመደበኛ ዘርፍ በሚፈጠሩ የስራ እድሎች የአዎንታዊ ድጋፍን አተገባበር መከታተልና ማስፈፀም፡፡
- ከአገር ውጪ በሚፈጠሩ የስራ እድሎች ሴቶችን በተገቢውና ህጋዊ በሆነ መንገድ አስፈላጊዉን ስልጠና ወስደው የስራ እድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡
- የድህነት ቅነሳ ፖሊሲዎቻችን በተለይ በከፋ የኑሮ ደረጃ (ድህነት) ላይ የሚገኙ ሴቶችን ከግምት ወስጥ በማስገባት እንዲዘጋጁ እና እንዲተገበሩ ማድረግ፡፡
- የሴቶችን የምጣኔ ሀብት አቅም ለማሳደግ የሚተለሙ መርሃ ግብሮች በሰው ሰራሽ እና በተፈጥሮ ሁኔታ የሚከሰቱትን አደጋዎች ለመቋቋም ሴቶችን ለድህነት ተጋላጭ ስለሚያደርጓቸው ይህንን ለመታደግ የሚያስችል የመንግስት የገንዘብ ቋት ማዘጋጀት፡፡
- መንግስት ከፍተኛ ቁጥር ላለው የወጣት የሕብረተሰብ ክፍል የስራ አጥነትን ለመቅረፍ በዘረጋው አሰራር መሰረት ሴቶችን እኩል ትኩረት በመስጠት በአግባቡ የስራ ዕድሉ ተጠቃሚ ማድረግ አለበት፡፡
- በድህነት ወለል የሚገኙ ሴቶችን በኢኮኖሚ ለመደገፍ በቂ የሆነ፣ ዝቅተኛ ወለድ እና በቂ የእፎይታ ግዜ ያለው ብድር አቅርቦት ሊተገበር ይገባል፡፡



# 5.የሴቶች ጥያቄዎች በፓለቲካ ተሳትፎ

ሴቶች ከወንዶች እኩል በተለያዩ ህይወታቸውን በሚመለከቱ ጉዳዮች በቤት ውስጥም ሆነ በውጪ ውሳኔ የመሰጠት እድሎቻቸው በጣም የተገደበ ነዉ፡፡ በተለይም መደበኛ በሆነዉ የመንግስት ኃላፊነት ሴቶች የውሳኔ ሰጪነት ተሳትፏቸዉ አነስተኛ ሆኖ ይታያል፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ደረጃ በ2010 ዓ.ም 27.9 በመቶ የነበረው በ2015 ዓ.ም 38.8በመቶ ደርሷል ፡፡የሴቶች በአስፈፃሚና በሌሎች ውሳኔ ሰጭነት ቦታዎች ያላቸው ተሳትፎ ባለፉት 3 አመታት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እምርታን ያሳየበት ጊዜ ነው፡፡ የሴት ፕሬዝዳንት፣ ሴት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት፣ ሴት የሚኒስትር መሰሪያቤት ኃላፊዎች በመሆን የጠቅላይ ሚኒስተሩ ካቢኔ 50 በመቶ ሴቶች መሆናቸው በኢትዩጵያ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ አዲስ እምርታ ነው፡፡

የሴቶችን የፓለቲካ ተሳተፎ ለማጠናከር በምርጫ ዙርያ የወጡት ህጎችና ፖሊሲዎች አሁንም በተጨባጭ በመዋቅር ደረጃ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ አይደሉም። ለምሳሌ በባለፈው ምርጫ በተወካዮች ምክር ቤት የተገኘው 38 በመቶ የሴቶች ተሳትፎ ገዢው ፓርቲ የውስጥ አሰራር ወይም ፈቃደኝነት ባስቀመጠው 40% ሴት እጩዎችን ማቅረብ ነው። ነገር ግን ይህ አስገዳጅ ሁኔታ ለሁሉም ፓርቲዎች በአገሪቷ የምርጫ የተቀመጠ ባለመሆኑ የሴቶች ተሳትፎ በተመራጭነት አሁንም በቂ አይደለም። እንዲሁም በምርጫ ወቅት የተለየ የበጀት ድጋፍ ለሴት እጩዎች በማዘጋጀት ለማበረታት ጥረት ተደርጓል፡፡ እነዚህ ጥረቶች ከላይኛው የፖለቲካ አመራር እስከ ክልል ዞን እና ወረዳ ድረስ ሴቶች በፖለቲካ እንዲሣተፉ እኩል በተዋረድ መቀመጥ ያለበት ነው፡፡

## የሴቶች ጥያቄዎች በፓለቲካ ተሳትፎ

- የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎን ለማጠናከር የተጀመሩ ጥረቶች በህግ እንዲደገፍ ያስፈልጋል፡፡
- የምርጫ ህጉ የሴቶች ቁጥርን ወይም ኮታ ወስኖ ማስቀመጠ አለበት፡፡
- አቅምና ብቃት ያላቸዉ ሴቶች በአመራር እርከን ውስጥ ወደ ላይኛዉ የአመራርነት ደረጃ እንዲመጡ የተለያዮ ድጋፎችና ጥረቶች መደረግ አለበት፡፡
- በማኅበረሰብ ዉሰጥ ያሉ ሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለመጨመር የግንዛቤ ማስጨበጥ ሰራ እና ምቹ የፖለቲካ ምህዳር መፈጠር ይኖርበታል፡፡
- የሴቶች የውሳኔ ሰጪነትን ለማሳደግ የተለያዩ ሴቶችን በሁሉም ዘርፍ የማብቃት ስራዎች መሰራት አለበት፡፡

# 6. ፆታዊ ጥቃት




በማኅበራዊ መስተጋብሮች ውስጥ የሴቶችና የወንዶችን ሁኔታ በምናይበት ጊዜ ወንዶች በብዙ መልኩ በተሻለ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፡፡ በተለያ በባህላዊ ተፅእኖዎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ሴቶች የበለጠ ተጎጂ ሆነው ይታያሉ፡፡ ፆታዊ ጥቃትም ይህ ሁኔታ ከሚገለፅባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡ ፆታዊ ጥቃት ብዙ አይነት መገለጫዎች ሲኖሩት በኢትዮጲያ ውስጥ በጣም ተስፋፍተዉ የሚታዩት የሴት ልጅ ግርዛት፣ ያለእድሜ ጋብቻ፤ የቤት ውስጥ ጥቃት፤መደፈር፤ ህገውጥ ዝውውር፣ በስነልቦና ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች፣ የኢኮኖሚ ጥቃቶችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ተፅእኖዎች ሴቶች ላይ ከፍተኛ የጤና፣ የስነልቦና እና የምጣኔ ሀብት ተደራራቢ ጉዳቶችን ያደርሳሉ፡፡ ባለፉት አስርት አመታት እነዚህን በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለመከላከል የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ ቆይቷል፡፡ ከነዚህም እርምጃዎች በዋናነት ጎጂ ልማዳዊ ድርጎቶችን ለማስቀረት በወንጀል ህጉ እንደ ወንጀል ተግባር መደንገጋቸው አንዱ ነው። ከዚህም የተነሳ እነዚህ ችግሮች መቀነስ ያሳዩ ቢሆንም አሁንም ብዙ ስራ ይጠይቃል፡፡

ግርዛትን በተመለከት ባለፍት ሁለት አስር አመታት 25 ሚሊዮን የሚሆኑ ታዳጊ ሴቶች በዚህ አስከፊ ሂደት ውስጥ ለማለፍ ተገደዋል፡፡ በተለይም በሶማሌና በአፋር ክልል ድርጊቱ 99በመቶ እና 91በመቶ ያህል ነው፡፡ UNICEF 2019 ዓ.ም ባወጣው ያለእድሜ ጋብቻ ጋር በተያያዘ ሪፖርት ላይ እድሚያቸው 18 ያልሞላ ሴት ህፃናት በገጠር አካባቢ በተለያዩ መንገድ የመዳር ሁኔታ ቁጥሩ መቀነስ ቢያሳይም እ.ኤ.አ በ2017 ዓ.ም 40በመቶ ሴት ልጆች 18 አመታቸው ሳይሞላቸው እንደተዳሩ የሚያሳይ ሲሆን ይህ ሁኔታም ለተለያዩ የጤና ዕክል ፤የአካልና የስነልቦና ጉዳት ይዳርጋቸዋል፡፡ ያለእድሜ ጋብቻም በተለይ በአማራ፣ በኦሮሚያ እና ጋምቤላ ክልሎች ላይ በሰፊው ይተገበራል።

በኢትዮጵያ ወንዶችን የበላይ በሚያደርገው አባታዊ ስርአት ምክንያት ማህበራዊ መስተጋብርና የሀይል ሚዛን በተለይም በትዳር ውስጥ በወንዶች የበላይነት የተያዘ በመሆኑ የቤት ውስጥ ጥቃት በብዛት በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች በሴቶች ላይ የሚፈጸም ተግባር ነው፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው እ.ኤ.አ በ 2016 ዓ.ም በተደረገው የስነ ህዝብና የጤና ዳሰሳ ጥናት ሴቶች በባሎቻቸው ሊደበደቡ ይገባቸዋል ተብሎ ሰፋ ባለው የማኅበረሰብ ክፍል እንደሚታሰብ አሳይቷል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚያመላክተዉ የሴቶች ጥቃት በማኅበረሰብ ዉስጥ በሰፊዉ የሚፈጸምና ተቀባይ መሆኑንም ጭምር ነዉ፡፡ በተጨማሪም ይኸዉ ጥናት ከ10 ሴቶች ውስጥ 3ቱ አካላዊ ወይም ወሲባዊ ጥቃት በህይወት ዘመናቸው እንዳጋጠማቸው ያሳያል።

## ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እየታዩ ያሉ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች

ባለፉት 5-10 አመታት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ አዳዲስ የጥቃት አይነቶች እየበዙ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም መካከል አሲድ መድፋት ፣በቡድን የሚፈፀም አስገድዶ መድፈር፣ በማኅበራዊ ድህረገፆች የሚደረጉ የተለያዩ የስም ማጥፋት፣ ማስፈራራት፣ ክብርን የሚነኩ ንግግሮችና ሁኔታዎች ይገኙባቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ የወሲብ ጥቃትን እንደ ግጭት መሳሪያ መጠቀም በቅርብ ጊዜ እየታዩ ያሉ የጥቃት አይነቶች ናቸው፡፡



# ሴቶችን በሚመለከት የወጡ ህጎች

በአገራችን በተለየ ሁኔታ ሴቶችን ከጥቃትና ከተለያዩ የመብት ጥሰት የሚጠብቁ ህጎች ወጥተዋል፡፡ ነገር ግን ማኅበረሰቡ ከተፃፉ ህጎች ይልቅ ለባህላዊ ህጎችና ልማዶች የተሻለ ስፍራ የመስጠትና ባልተጻፉ ግን ማኅበረሰቡ በደነገጋቸው ህጎችና ደንቦች መተዳደርን ይመርጣል፡፡የተሻሻለው የወንጀል ህግ በተለይም የሴት ልጅ ግርዛት ፣ያለእድሜ ጋብቻ ፣ጉልበት ብዝበዛ፤ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን በተመለከት አንቀፆችና ቅጣቶች አስቀምጧል፡፡



ነገር ግን የወሲብ ጥቃትና የቤት ውስጥ ጥቃትን በተመለከተ የህግ ክፍተት ያሳያል ወይም እነዚህን ጉዳዮች በተመለከተ የተቀመጠ የህግ አንቀፅ የለም፡፡ በተጨማሪም የቤተሰብ ህግ የጋብቻ እኩልነትና በፍቺ ግዜ ሂደቱንና የሀብትና ንብረት ክፍፍልን ሁኔታዎች በተሻለ መልኩ የሴቶች እኩልነትን ያረጋገጠ ነው፡፡ በሌላ በኩል የቤተሰብ ህግን የማውጣት ስልጣን ለክልሎች የተሰጠ ኃላፊነት በመሆኑ ሁሉም ክለሎች ይህን ህግ የሴቶች እኩልነትና ፍላጎት ባሟላ መልኩ ሲያወጡ አይታይም። ለምሳሌ አፋርና ሶማሌ ክልሎች ገና የቤተሰብ ህግ የሌላቸው ሲሆን እየተዳደሩ ያሉት በ1952 ዓ.ም በወጣውና ብዙ የህግ ክፍተት ባለው እንዲሁም ሴቶች ላይ በጣም ብዙ ተጽዕኖ በሚያሳድረው ህግ ነው፡፡

## በፆታዊ ጥቃት ዙሪያ የሴቶች ጥያቄዎች

- የሴቶች ጥቃትን በተመለከተ ከማኅበረሰብ በኩል ያለውን ምልከታ በተለያዩ የትምህርት፣ የግንዛቤ ማስጨበጫና የህግ እርምጃዎች መደገፍ አለበት
- የሴት ልጅ ግርዛትና ያለእድሜ ጋብቻን ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት የተጀመሩ እንቅስቃሴዎች (የድርጊት መርሀ ግብር) በበጀትና በተጠያቂነት አሰራር ተደግፈዉ እንዲፋጠኑ ማድረግ፡፡
- በቅርብ ጊዜ እየታዩ ያሉ በሴቶች ላይ የሚደርሱ የጥቃት አይነቶች የህግ አንቀፅና ተገቢው የሆነ የማስተማሪያ ቅጣቶች ማውጣት፡፡
- ፆታዊ ጥቃትን በተመለከተ የወጡ ህጎችን የሚተረጉም የህግ መርሀ ግብር /ፖሊሲ ማዘጋጀትና በየእርከኑ የተጠያቂትን አሰራር መዘርጋት፡፡
- ጾታዊ ጥቃትን በተመለከተ የወጡ ህጎችን በአንድ ላይ በማስቀመጥ የጎደሉትን በሟሟላት፣ አስፈላጊውን መርሃ ግብር እና ፖሊሲ በማዘጋጀት እና በመተግበር ፆታዊ ጥቃትን መታገል፡፡
- የህግ አስፈፃሚ አካላትን የግንዛቤ እጥረት በተከታታይና ወጥ በሆነ መልኩ መቅረፍ፡፡
- ለፆታዊ ጥቃት ምላሽ የሚሰጡ የአገልግሎት ዘርፎችን ማስፋፋት፥ በበጀት በሰዉ ኃይልና አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ሁሉ በማሟላት ፆታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች አስፈላጊ አገልግሎቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡
- በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የሚመራው በሴቶች ላይ የሚደርሱ የፆታዊ ጥቃቶችን በመከላከልና ምላሽ በመስጠት ዙሪያ የሚሰሩ አካላትን የሚያቀናጀዉ ግብር ኃይል እንዲጠናከርና የጎላ ሚና እንዲኖረዉ መደረግ አለበት፡፡
- ዜጎችን በህገ ወጥ መንገድ በሚያዘዋውሩ ደላሎች ላይ የሚወሰደው እርምጃ ጥብቅ ሊሆን ይገባል። በመንግስት ህጋዊ እውቅና የሚሰጣቸው ደላሎች (ኤጀንሲዎች) ስራውን በትክክል የመስራት አቅም ያላቸው መሆኑ መመርመር አለበት፡፡
- በፆታዊ ጥቃት ዙሪያ ኢትዮጲያ የፈረመቻቸዉና ያፀደቀቻቸዉ አለምአቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚያስችል ስርአት መዘርጋት፡፡
- በሴቶች ላይ የሚደርስ ፆታዊ ጥቃትን ለማስቀረት የወጡ ህጎችን ተፈጻሚ ማድረግ እና የተጠያቂነት አሰራር መዘርጋት።
- በስራ ቦታና በትራንስፖርት አካባቢ የሚደረጉ ወሲባዊ ትንኮሳዎችን ለመከላከል ግንዛቤ የመፍጠር ስራዎችን በወጥነት መስራትና የፖሊስ አገልግሎቶችን ማስፋፋት፡፡
- በታዳጊ ክልሎች ያለተጠያቂነት የሚፈፀሙ እንደ ጠለፋ፣ በጋብቻ ላይ ጋብቻ፣ ውርስ ጋብቻ አና ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መስራት እና ተጠያቂነትን ማስፈን፡፡
- የአፈጻጸም ችግሮችን በመቅረፍ ፆታዊ ጥቃትን ማስቀጣት እና የሚሰጡ ውሳኔዎች መቀጣጫ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል።
- ያለ እድሜ ጋብቻን ለማስቀረት በአገሪቱ የተጀመረውን የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡
- ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ሴቶች ለመደገፍ የሚቋቋሙ ጊዜያዊ መጠለያዎች በቁጥር አነስተኛ ከመሆናቸው በተጨማሪ በሲቪል ማህበራት ብቻ የተያዙ በመሆናቸው መንግስት ይህንን ኃላፊነት ወስዶ መጠለያዎች በሁሉም አካባቢዎች ማቋቋም አለበት፡፡
- ፆታዊ ጥቃት ላይ ምላሽ ለመስጠት የሚቋቋሙ የአንድ መስኮት አገልግሎቶች በየአካባቢው በበቂ ቁጥር ማቋቋም፣ ያሉቱም የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ መደረግ አለበት፤
- ፆታዊ ጥቃት ላይ ምላሽ የሚሰጡ ተቋማትን የግንኙነትና የቅብብሎሽ (Referal linkage) ስራ ማጠናከርና ተጠያቂነትን መፍጠር፡፡

# 7.የመሰረተ ልማት ተደራሽነትና የሴቶች ጥያቄዎች

በመግቢያ ክፍል እንደተጠቀሰው ሴቶች በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ የኖራሉ ነገር ግን እጅግ በከፋ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሴቶችን በተለየ ሁኔታ መመልከት ያስፈልጋል እነዚህም በወሲብ ንግድ የሚተዳደሩ ፣በጎዳና ላይ ያሉ አካል ጉዳተኞች ሴቶች ከ HIV ጋር እና ከሌሎች ተጓዳኝ በሽታዎች ጋር በዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ምንም እንኳን ወንድ አቻዎች በተለያዩ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ቢገኙም የሴቶች ሁኔታ የከፋ የሚሆነበት ሁኔታ ይታያል፡፡

የመሰረተ ልማት ተደራሽነትና የሴቶች ጥያቄዎች

- በገጠር አካባቢዎች የዉሃ፣ መንገድና መብራት መሰረተ ልማት ተደራሽነት ለሴቶች ካለዉ ጠቀሜታ አንጻር መስፋፋት አለበት
- የሚገነቡ መሰረተ ልማቶች የሴቶችን አንገብጋቢ ፍላጎቶች ያማከሉ መሆን አለባቸዉ
- መሰረተ ልማቶችን በመገንባት ሂደት ውስጥ የሴቶች ተሳትፎና ውሳኔ ሰጪነት መረጋገጥ አለበት

# 8. በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሴቶች

በዚህ ማኒፌስቶ መግቢያ ላይ እንደተጠቀሰው ሴቶች በተለያዩ ስፍራዎችና የአኗኗር ሁኔታ ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን እጅግ በከፋ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሴቶችን በተለየ ሁኔታ መመልከት ያስፈልጋል፤ እነዚህም በወሲብ ንግድ የሚተዳደሩ ፣በጎዳና ላይ ያሉ፤ አካል ጉዳተኞች ሴቶች፤ ከHIV ጋር እና ከሌሎች ተጓዳኝ በሽታዎች ጋር በዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ፤ ሴቶችን በአስቸጋሪ ሁኔታ የሚገኙ ተብለው በዚህ ማኒፉሰቶ ውስጥ ተካተዋል፡፡ ምንም እንኳን ወንድ አቻዎች በተመሳሳይ በተለያዩ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ቢገኙም የሴቶች ተጎጂነት ከወንዶቹ በበለጠ የከፋ የሚሆነበት ሁኔታ ይታያል፡፡

## 8.1 አካል ጉዳተኛ ሴቶች

በአገራችን ውስጥ በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ በሆኑ ምክንያቶች የተለያዩ አይነት የአካል ጉዳት ያጋጠማቸው የህብረተሰቡ ክፍሎች 17 በመቶ ወይም 15 ሚሊዮን ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ ሴት የአካል ጉዳተኞ በበለጠ ለተለያዩ ችግሮች ተጋልጠው ይገኛሉ፡፡ ሴት አካል ጉዳተኞች በተለየ ሁኔታ ለፆታዊ ጥቃትና ለጉልበት ብዝበዛ ተጋላጭነታቸውም ከፍ ያለ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ያለምንም ማዳላትና ልዩነት ለሁሉም እንደየፍላጎቱ አገልግሎቶችን ለማቅረብ የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌም በትምህርት በኩል በልዩ ፍላጎት የትምህርት ዘርፍ መምህራንን ለማፍራት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችና ሴት አካል ጉዳተኞች የትምህርት እድል እንዲያገኙ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በዋናነት የሚጠቀሱ ሲሆን ይህንንም አጠናክሮ ለማስቀጠል እየተሰራ ይገኛል፡፡

## 8.2 ከኤች አይቪ ጋር የሚኖሩ ሴቶች

በኢትዩጵያ ውስጥ እ.ኤ.አ በ2019 ዓ.ም በተከቀመጠው መሰረት 670000 የሚሆኑ ዜጎች ከHIV ጋር ይኖራሉ፡፡ ከነዚህ ዜጎችም ውስጥ ከ15 አመት በላይ የሆኑ 390000 ሴቶች ከቫይረሱ ጋር እየኖሩ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ አብዛኛዎች በከፋ ድህነት ውስጥ ሆነው ኑሮን እየገፉ የሚገኙ ሲሆን ምንም እንኳን የፀረ ኤች አይ ቪ መድሀኒት በነፃ የሚገኝ ቢሆንም ሴቶች ባለባቸው ድርብርብ የኢኮኖሚ የማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጫናዎች ምክንያት ከHIV ጋር የሚኖሩ ሴቶች ብዙ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል።

የኤች አይ ቪ ስርጭትን በኢትጵያ ስንመለከት፣ በአሁኑ ሰአት ተጋላጭ ናቸው ተብለው ከተለዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች መካከል በዝቅተኛ ኑሮ ውስጥ የሚገኙ ሴቶች፣ ከትምህርት ቤት ውጪ ያሉ ወጣት ሴቶች፣ በከተማ አካባቢ በወሲብ ንግድ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሴቶች ላይ ያለው ስርጭት በጣም ከፍተኛ ነው ይኸውም እስከ 28 በመቶ ይደርሳል፡፡

## 8.3 በአርብቶ አደር አካባቢ የሚኖሩ ሴቶችና ታዳጊዎች

በኢትዮጵያ ውስጥ ከ12-15 ሚሊዮን የሚሆነው ህዝብ በአርብቶ አደር የማኅበራዊ መሰረት በ7 ክልሎች ውስጥ ይኖራል፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ ሴቶችም ዘርፈ ብዙ ከሆኑ ችግሮች ጋር ይኖራሉ፡፡ ትምህርት የማግኘት እድላቸው በጣም አነስተኛ መሆን ለተለያዩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የተጋለጡ ያደርጋቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለድርብርብ የስራ ጫናም ይዳረጋሉ፡፡ የማይከፈልበት የቤት ውስጥ ስራ ጫናውም በሌላ አካባቢ ከሚኖሩ ሴቶች በተለየ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ እንጨት መልቀም፣ እንስሳት መንከባከብ፣ ምግብ ማዘጋጀት፣ውሃ መቅዳትና የእንስሳት ግጦሽ ፍለጋን ምክንያት በማድረግ ከቦታ ቦታ በሚደረግ እንቅስቃሴ ወቅት ለቤተሰቡ መጠለያ ቤት የመስራት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ከሁሉም በላይ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ያለው ማኅበራዊ መስተጋብር እሴቶች ለሴቶችና ለታዳጊ ሴቶች የሚሰጠው ቦታ ከወንዶች አንፃር በጣም አነስተኛ ነው፡፡ የታዳጊ ሴቶች ህይወት በቀጥታ የሚያያዘው ከሚመሰርቱት ጋብቻ ነው፡፡ ለምሳሌ የመኖሪያ ስፍራን ከመወሰን ጀምሮ፣ ውርስ የማግኘት ፣የትምህርት ዕድል እና የስነ ተዋልዶ ጤና ላይ ሁሉ በባሎች ፣በአባቶችና ፣ወንድሞች ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በአርብቶ አደር አካባቢ ያሉ ሴቶች እጅግ ፈታኝ በሆነ አካባቢና የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ ፡፡



## 8.4 ከገጠር ወደ ከተማ ፈልሰዉ የመጡ ታዳጊ ሴት ልጆች

ኢትዮጵያ ባለፉት 10-15 አመታት ወዲህ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደርግ ፍልሰት በጣም ጨምሮ ይታያል፡፡ በተለይም ወጣቶች በድህነት ምክንያት ስራ ፍለጋ ፣ያለእድሜ ጋበቻን ለማምለጥ ፣የተሻለ የትምህርት እድልን ፍለጋ ብዙ ሴቶች ልጃገረዶችም በህገወጥ ደላሎች በመታለል ወደ ከተሞች ይፈልሳሉ፡፡ በከተሞች አካባቢም ተሰማርተው የሚገኙባቸው ስራዎችም ዝቅተኛ ክፋያ የሚያስገኙ ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ በቤት ስራተኝነት ፣በቀን ስራተኝነት ፣በጎዳና ላይ ንግድ ፣በወሲብ ንግድ ፣በአስተናጋጅ እና የመሳሰሉት የስራ አይነቶች ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ደግሞ ብዙዎቹ ለፆታዊ ጥቃት በከፈተኛ ሁኔታ ተጋልጠው ይገኛሉ፡፡ በሚሄዱባቸውም ከተሞችም መደበኛ ነዋሪዎች ስላልሆኑ የነዋሪነት መታወቂያ በማውጣት የተለያዩ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ሲያገኙ አይታዩም ፡፡

## 8.5 ተፈናቅለው በመጠለያ ውስጥ የሚገኙ ሴቶች

በኢትዮጵያ ባለፉት 3 አመታት በተከሰቱ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ቁጥራቸው 3.2 ሚሊዮን የሆኑ ተፈናቃዮች በተለያዩ የመጠለያ ጣቢያዎች ይገኛሉ፡፡ እንደነዚህ አይነት መፈናቀሎች እጅግ የበዛ ጉዳት የሚያስከትሉት ሴቶችና ህፃናት ላይ ነዉ፡፡ በጊዜያዊ መጠለያ ውስጥም በቂ ምግብና ውሃ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች ስለማያገኙ ብዙ ችግሮች ያጋጥማቸዋል፡፡ በተጨማሪም ለፆታዊ ጥቃት የተጋለጡ እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ የጤና፤የትምህርትና የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴዎችም ስለሚገቱ በተለይም ለረጅም ጊዜ መጠለያ ጣብያ ውስጥ የሚቆዩት እነዚህን አገልግሎቶች የሚያገኙበት ሁኔታ ያነሰ ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት በመጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የሚኖሩ ሴትፕች በተለየ ሁኔታ ለከፍተኛ ችግር የተጋለጡ ናቸው።

## በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሴቶች ጥያቄዎች

- በተለያዩ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ላሉ ሴቶች ፍላጎታቸውንና ችሎታቸውን ያማከሉ የተለያዩ ፕሮግራሞች ተቀርፀው ትኩረት እንዲያገኙና ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረግ አለበት፡፡
- ከተለያዩ የአካል ጉዳት ጋር የሚኖሩ ሴቶችን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የጤና እና የትምህርት አገልግሎቶችን ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡
- የሚሰሩ መስረተ ልማቶች የአካል ጉዳተኛ ሴቶችን ሁኔታ ያገናዘቡ እንዲሆኑ አስገዳጅ ማድረግ የተደረጉትም በአግባቡ መስራታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡
- አካል ጉዳተኛ ሴቶች ካሉባቸው የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች አንፃር የተለየ ትኩረት በማድረግ ህይወታቸውን ለማሻሻል ጥረቶች መቀጠል አለባቸው፡፡
- ሴቶች በማንኛም የስራ መስክ ብቁ ተወዳዳሪነት ሊያጎናፅፋቸው በሚችሉ የትምህርትና የስልጠና መስኮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረግ አለበት፡፡
- በሁሉም ብሄራዊ አጀንዳዎች የአካል ጉዳተኛ ሴቶች ጉዳይ እንዲነሳ ማድረግና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚወጡ ህጎችና ስምምነቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በሰፊዉ በመስራት ተግባራዊ እንዲሆኑ መደረግ አለበት፡፡
- ከኤች አይቪ ጋር የሚኖሩ ሴቶች በተለይም ህፃናት ልጆችን ይዘው በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴቶች በአካባቢያቸው በሚጀመሩ ስራዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- በአርብቶ አደር አካባቢ ለሚኖሩ ሴቶች ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በተለይም ከግርዛትንና ያለ እድሜ ጋብቻ እንዲጠበቁ የተለየ ትኩረት ያስፈልጋል፡፡
- ከገጠር ወደ ከተማ ባለማወቅና በመታለል የሚመጡ ሴት ታዳጊ ልጆችን በተለየ ሁኔታ ትኩረት በማድረግ ሊደርሱባቸው ከሚችሉ የተለያዩ ጥቃቶች እና አደጋዎች መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡
- በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ምክንያት በግዚያዊ መጠለያ ውስጥ ላሉ ሴቶችና ህፃናት የሚደረጉ ድጋፍ ፍላጎቶችን በመለየት ሊሆን ይገባል፡፡ ከምግብና መጠለያ ባሻገር የንፅህና መጠበቂያ፣ የተዋልዶ ጤና አግልግሎቶችን በተለይም የእርግዝና ክትትል፤ የማዋለድና የቤተሰብ እቅድ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡
- በወሲብ ንግድ ለሚተዳደሩ ሴቶች አማራጭ የስራ እድሎችን መፍጠርና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡
- ከስደት ተመላሾች በከፍተኛ ችግር ላይ የሚገኙ በመሆናቸው በመንግስት መደገፍ አለባቸዉ ። ለዚህም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሚያደርጉት ጥረት በተጨማሪ መንግስት መልሶ ማቋቋሚያ መጠለያዎች በመዘርጋት አገልግሎት ሊያገኙ ይገባል፡፡
- የተፈናቃይ መጠለያ ጣቢያዎች ትክክለኛ አገልግሎቶች እንዲሠጡ የወንዶች እና ሴቶች ክፍሎችን በመለየት አስፈላጊው የምግብና የህክምና አገልግሎት እንዲኖራቸው መደረግ አለበት፡፡
- በህግ ጥላ ስር ላሉ ሴቶች አስፈላጊዉን ትኩረት በተለይም ልጆቻቸዉ ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ፡፡
- ፍርደኛ ሴቶች ህፃናት ልጆቻቸውን ከማረምያ ግቢ ውጭ የሚያሳድጉበት የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር ይደረግ።
- በታዳጊ ክልል ያሉ ሴቶች በመሠረተ ልማት በጀት በፕሮግራሞችና በፖሊሲዎች ተጨማሪ ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

# 9. ሴቶች የአካባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥ



ማኅበረሰባችን ውስጥ ባለው የስራ ክፍፍል ምክንያት ሴቶች ከአካባቢያዊ ስነምህዳር ጋር የተለየ ቁርኝት አላቸው፡፡ በተለይም የእለት ተእለት ምግብ ለማብሰል የሚስያፈልገውን የማገዶ እንጨት መሰብሰብ፣ ውሃ መቅዳት በዋናነት በየቀኑ የሚያከናውኗቸው ስራዎች ናቸው፡፡ በአሁኑ ሰአት የደኖች መራቆትና የዓለም ሙቀት መጨመር በከፍተኛ በገጠራማው ክፍል የሚገኙ ሴቶችን በቀጥታ ይጎዳቸዋል፡፡ በአቅራቢያቸው ያገኙአቸው የነበሩ የማገዶ እንጨት እና ውሃ በአካባቢ መራቆት ምክንያት ሴቶች ተጨማሪ ጉዞ እንዲያደርጉ እያስገደዳቸው ይገኛል፡፡

በተጨማሪም ታዳሽ የሃይል ምንጮች የሚገኙ ለምሳሌ የኤሌትሪክ ሀይል፣ ማገዶ ቆጣቢ፣ ጭስ የሌላቸው ምድጃዎች ሙሉ በሙሉ ለሁሉም ተደራሽ ባለመሆናቸዉ በተለይም በገጠር የሚኖሩ ሴቶች ለድርብርብ የስራ ጫና ተዳረገዋል፡፡ ሴቶች በአካባቢ ጥበቃ ስራ ከፍተኛ ተሳተፎ ያደረጋሉ፡፡ ችግኝ በማፍላት፤በመትከል ፣እርከን በመስራት ፣የመስኖ ቦይ በመቆፈር አካባቢ ጥበቃ ላይ የጎላ ድርሻና ተሳትፎ ቢኖራቸውም ተሳትፏቸው ግን በአግባቡ እውቅና ሲሰጠው አይታይም፡፡

## በአካባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥ ዙሪያ የሴቶች ጥያቄዎች

- በገጠር አካባቢዎች ምግብ ለማብሰል የሚዉለዉን ማገዶ እንጨት በኤሌትሪክ ኃይል በመተካት የሴቶችን የስራ ጫናና የጤና ሁኔታ መሻሻል አለበት፡፡
- ሴቶች በአካባቢ ጥበቃ ዘርፍ እንደ ዋና ተዋናይ ሊታዩ ይገባል፡፡
- ሴቶች አካባቢን ለመጠበቅ በሚደረጉ ስራዎች ውስጥ ፍላጎታቸዉ መካተት አለበት፡፡
- በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎች ሴቶችንና ህፃናት የበለጠ ተጎጂ ስለሚያደርጉ ምላሽ ለመስጠት የሚደረጉ ጥረቶች የነሱን ፍላጎት ያማከለ መሆን አለበት፡፡
- የአካባቢ ጥበቃን መሰረት አድርገዉ በሚፈጠሩ የስራ እድሎች ሴቶችም እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡

# 10. የሴቶች ጥያቄ በመልካም አስተዳደር፣ በሠላም እና ደህንነት

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ያለችበት የጸጥታና ሰላም ሁኔታ ሴቶችን ለተለያዩ ችግሮች እያጋለጠ ይገኛል። ይህን በተመለከተም ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ችግሩን ሊፈታ የሚችል እርምጃ ወይም ስልት በመንደፍ መንግስት ችግሮችን ሊፈታና የሴቶችን ሁኔታ ሊያይ ይገባል። የመልካም አስተዳደር እጦት፤ ሴቶች ፍትህ እና ሌሎች አገልግሎቶችን እንዳያገኙ ያደርጋል። ይህንን የሴቶችን ተጋላጭነት በግጭት ውስጥ በዘላቂነት ለመፍታት መንግስት አስፈላጊውን ተግባርና ስልት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

- ሴቶች መልካም አስተዳደርን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ ዋና ተሳታፊ መሆን አለባቸው፡፡
- የሠላም እጦት በተደጋጋሚ የሚከሰትባቸዉ ቦታዎችን መንግስት ሰላምን በማስከበር ለሴቶችና ለህጻናት ልዩ ጥበቃ ማድረግ አለበት፡፡
- በእርቅና በማስማማት ስራዎች ላይ ሴቶች እኩል ውክልና ሊኖራቸው ይገባል፡፡
- በሰላም ውይይቶች ላይ ሴቶች መሳተፍና ዉሳኔ እንዲሰጡ መደረግ አለበት፡፡
- በግጭት ወቅት ለሰላማዊ ሰዎች በተለይም ለሴቶችና ህፃናት የሚደረገው ጥበቃ ስርዓትና ተጠያቂነት ለበጅለት ይገባል።

# 11.የሴቶችን ጥያቄ ለመመለስ ያሉ ተቋማትና አደረጃጀቶችን በሚመለከት የሴቶች ጥያቄዎች

በእያንዳንዱ የመንግስት ሴክተር መስሪያ ቤቶች ዉስጥ ተቋቁመዉ የሚገኙት የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬቶች በተለያየ የስራ ዘርፍ ውስጥ ሴቶች ህፃናትና ወጣቶችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚለዩና የሚከተታሉ ተቋማዊ አደረጃጅቶች ናቸዉ፡፡

እነዚህ ተቋማዊ አደረጃጅቶች መኖራቸው እጅግ ጠቃሚ ቢሆንም በየሴክተር መስሪያ ቤቶች ውስጥ ያላቸው ሚና የጎላ አይደለም ፡፡ የበጅት አለመመደብ ፣የአቅም ማነስ፣ የሰው ኃይል በበቂ ሁኔታ አለመኖር፣ ክፍሎቹ በብቃት የሴቶችን ጉዳይ የማካተት ስራን እንዳይሰሩ ተግዳሮት ሆነዋል ፡፡ እነዚህ ተግዳሮቶች በክልል እና ወረዳ ደረጃ በተዋቀሩ የሴቶች ጉዳይ ቢሮዎችም የበለጠ ጎልተው ይታያሉ። በተለይም ክልሎች በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት መዋቅሮችን የመክፈትና የመዝጋት ስልጣን ስላላቸው ይህ ክፍል በአንዳንድ ክልሎች አካባቢ የመዘጋት ሁኔታ ይታያል፡፡

በፌደራል ደረጃም የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ሚንስቴር ብዙ ዉጤታማ ስራዎችን እየሰራ ቢገኝም ሦስት ትልልቅ የተለያየ እይታ የሚጠይቁ ጉዳዮችን እነዚህም ሴቶች፥ ህፃናትና ወጣቶች በአንድ ጠቅልሎ የያዘ በመሆኑ ለስራ አፈፃፀምና ውጤታማነት እንደ ተግዳሮት ሆኖ ሊቆጠር ይችላል፡፡

## የሴቶችን ጉዳይ ተቋማዊ በማድረግ ዙሪያ ያሉ ጥያቄዎች

- በአሁኑ ጊዜ በየሴክተሩ ተቋቁመዉ ያሉ የሴቶች ህፃናት ወጣቶች ዳይሬክቶሬቶች ተጠናክረዉ የተሰጣቸውን ኃላፊነት መወጣት እንዲችሉ በበጀት፤በሰዉ ኃይል፤በተጠሪነትና በዉሳኔ ሰጪነት አስፈላጊዉ ትኩረት ሊሰጣቸዉ ይገባል፡፡
- በክልሎች አካባቢ የሚታየዉ መዋቅሩን የመዝጋትና ባለሙያ ያለመመደብ ሁኔታ የመዋቅሩ አስፈላጊነት ታምኖበት እንዲከፈትና የሰዉ ኃይል እንዲመደብ መደረግ አለበት፡፡
- የሴቶች፤ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስትር ሌሎች ተቋማትን የመከታተልና ተጠያቂ የማድረግ ስልጣን እንዲኖረዉ ያስፈልጋል፡፡
- ሶስት ትልልቅ ጉዳዮችን የያዘዉ ሚኒስትር መስሪያ ቤት አወቃቀሩ እንዲፈተሽና ውጤታማ የሚያደርግ አወቃቀር ተዘርግቶ ስራ ላይ እንዲዉል፡፡
- ስርአተ-ፆተን መሰረት ያደረገ የበጀት አመዳደብ ስርአትን ማጠናከርና በሁሉም ሴክተር ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፡፡
- የሴቶች ማኅበራት የሚቋቋሙት አባሎቶቻቸውን መብት ለማስከበር ነው፡፡ስለዚህም የሴቶች ማኅበራትና አደረጃጀቶች ነፃ፣ ገልለተኛ እና የራሳቸው ድምጽና ውክልና እንዲኖራቸው የህግና የተግባር እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው።




## 12. በመገናኛ ብዙሀን ዙሪያ የሴቶች ጥያቄዎች

- መገናኛ ብዙኃን የሴቶችን ሀሳቦችና ፍላጎቶች የሚያንጸባርቁ ጉዳዮች ላይ አትኩረው መስራት አለባቸው፡፡
- መገናኛ ብዙሀን የስርአተ ጾታ እኩልነትንና ፍትሀዊነትን ባገናዘበ መልኩ ፕሮግራሞችንና ማስታወቂያዎችን ማቅረብ አለባቸው፡፡
- በመገናኛ ብዙሀን ውስጥ የሚሰሩ ብቃትና የትምህርት ዝግጅት ያላቸው ሴት ጋዜጠኞች የስራ እድገትና አመራር የመሆን ቦታ መሰጠት አለበት፡፡
- የመገናኛ ብዙሃን ሥራዎች ሴቶች በማኅበረሰብ ያላቸው ቦታ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ በመሆናቸው፤ ሴቶችን የሚያንኳስሱ ፕሮግራሞችን የሚያቀርቡ መገናኛ ብዙሃን ለህግ የሚቀርቡበት መንገድ መኖር አለበት፡፡

# 13. ሌሎች ጉዳዮች

## የፍትህ ተደራሽነት

ሴቶች ፍትህ እንዳያገኙ ከሚያደርጉ ጉዳዮች መካከል፣ ፍትህ ለማግኘት የሚያስፈልገው ወጪ፣ የመረጃ እጥረት፣ የህግ ድጋፍ አለመኖርና የማኅበረሰብ ለሴቶች መብት ያለው አመለካከት አናሳ መሆን ይገኙበታል። የዚህም ዋነኛ ምክንያቶች ህጉ በሚገባ ተፈፃሚ አለመሆን፣ በሴቶች መብት መከበር ጉዳይ ላይ ተጠያቂነት ማነስና የፍትህ ተደራሽነት አለመኖር ናቸው። ፍትህን የተመለከተ ማስረጃና መረጃ አሰባሰብ ላይ ያለው የጊዜና የሀብት ውስንነት ሌላው ሴቶችን ፍትህ እንዳያገኙ ትልቅ ተግዳሮት ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ለምሳሌ የአባትነትን ጥያቄ ለማረጋገጥ የሚጠየቀው የድ.ኤን.ኤ ምርመራ በሀገሪቱ መዲና አዲስ አበባ ብቻ የሚካሄድ በመሆኑ ሴቶችን ከአቅማቸው በላይ ለሆነ ወጪ ያጋልጣቸዋል። በዚህም ምክንያት ሴቶች ልጆቻቸውን ያለአባት ብቻችዉን ለማሳደግ ይገደዳሉ። የመሬትና ሀብት ክፍፍል ጉዳይን በተመለከተ የፍትህ ሂደቱ በጣም ረጅም ጊዜ ስለሚወስድ ሴቶች ለብዙ እንግልት ይዳረጋሉ፡፡

የፍትህ ተደራሽነትን በተመለከተ እስካሁን በመንግስት በኩል የተቋቋሙ የተለያዩ ችሎቶች ለሴቶች ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎትንም ተደራሽ ለማድረግ አበረታች ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

## በፍትህ ተደራሽነት የሴቶች ጥያቄዎች

- የፍትህ ተድራሽነት፣ በንብረት ክፍፍል፣ በፍቺ፣ በመሬት ባለቤትነት ጥያቄዎች ዙሪያ ተፈጻሚ መሆን አለበት።
- ከጾታዊ ጥቃት ጋር ተያይዘው ተጠቂዎች መረጃ እንዲያቀርቡ የሚጠየቁበት ሁኔታም አግባብ የሆነ ፍርድ እንዳያገኙ እና ለሌሎች መቀጣጫ እንዳይሆኑ አድርጓል፡፡
- የፍትህ ተደራሽነቱ በሁሉም ክልሎች በየደረጃው መፈጸም ይኖርባቸዋል።
- በፆታዊ ጥቃት የተጀመረው ልዩ ችሎት፣ በመሬትና ሀብት ክፍፍል ጉዳይም የተለየ ችሎት መኖር አለበት፡፡
- የህግ ሂደቱን ባልተንዛዛ መልኩ በአጭር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ እንዲያገኙ ማድረግ፡፡
- ሴቶች ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎትን በየአካበቢው እንዲያገኙ እንዲሁም ለተበዳዮች አመቺ የሆነ የፍርድ ሂደት እንዲኖር ያስፈልጋል፡፡
- በሴቶች መብት ላይ የሚሰሩና የሴቶች መብት ተሟጋቾች ግለሰቦች ከሚደርስባቸዉ ጥቃት መንግስት የህግ ከለላ ማድረግ አለበት፡፡

# 14. ማጠቃለያ

የሴቶች የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ የፖለቲካ፣ የሠላም እና ደህንነት ጥያቄዎች የሰብዓዊ መብት ጉዳይ እንደመሆናቸው መጠን በመንግስት ምስረታ እና አስተዳደር የአንበሳውን ድርሻ ሊይዙ ይገባል። ለዚህም በምርጫ የሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የግል ተወዳዳሪዎች ይህንን ጉዳይ እንደዋና አጀንዳቸው አድርገው በምመልከት በፕሮግራሞቻቸውና በፖሊሲያቸው ውስጥ እንደ አንድ የውጤት ግብ ሊያቅዱት ይገባል። ከዚህም ባለፈ በምርጫው ተወዳድሮ ስልጣን የሚይዘው ፓርቲ በዚህ ማኒፌስቶ የተዘረዘሩት ዋና ዋና የሴቶች ጥያቄዎችና የፆታ እኩልነትን ለማስፈን ቁልፍ ተብለው የተለዩትን ጉዳዮች ትኩረት በመስጠት አስፈላጊውን የፖሊሲ፣ የህግ፣ የማስፈፀሚያ ስልት፣ በጀትና፣ መዋቅር መድቦ ምላሽ እንዲሰጣቸው ይጠበቃል።

ነገር ግን እነዚህ በማኒፌስቶ የዘረዘርናቸው ዋና ዋናዎቹን ብቻና እስካሁኗ ሰዓት ያሉት ተመርጠው የቀረቡ እንደመሆኑ ጉዳዮቹ በትንሹ መሟላት ያለባቸው ናቸው። ስለዚህም በሚሰጡት ምላሾች ሌሎችንም ዝርዝር ጉዳዮችና በየወቅቱ የሚነሱ የሴቶችን ህልውና እና እድገት የሚገዳደሩ ሁኔታዎችን ያገናዘበና መብትን መሠረት ባደረገ መልኩ እንዲተገበሩ እናሳስባለን።

ባጠቃላይ ሴቶች በቤታቸው፣ በአካባቢያቸውና በሀገር ደረጃ ያደረጉትና እሁንም እያደረጉት ያሉት ትግል እስካሁን በእኩልነት ዙሪያ የመጡትን ድሎች አስገኝቷል። በዚህ ረገድ በመንግስት የተወሰዱ በጎ የፖለቲካ ውሳኔና እርምጃዎች እያደነቅን አሁንም ያልተመለሱት ጥያቄዎች ላይ ችግሮችን ለመፍታት የሴቶች መብቶች በሙልአት ይከበሩ ዘንድ፣ በልማትና በውሳኔ ሰጪነት ተሳታፊነታቸው ይረጋገጥ ዘንድ፣ ደህንነታቸው ዋስትና ያገኝ ዘንድ አሁንም የበለጠ ጥረት፣ የበለጠ ተግባርና ውጤት ከፓርቲዎችና ከመጪው መንግስት እንጠይቃለን።

ይህ የኢትዮጵያ ሴቶች ማኒፌስቶ ስማቸው ከታች በተዘረዘሩ የሲቪል ማኅበራት በጋራ ተዘጋጀ

ግንቦት 2013 ዓ.ም

1. የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት (ኢሴማቅ)
2. ሣራ ፍትህ ከሁሉም የሴቶች ማኅበር
3. ሴታዊት የበጎ አድራጎት ድርጅት
4. ሲቁ የሴቶች ልማት ማህበር
5. የሴቶች ይችላሉ ማኅበር
6. ፋሚሊ ሰርቪስ አሶሴሽን
7. የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሞያ ሴቶች ማኅበር
8. የኢትዮጵያ ሴቶች ሃኪሞች ማኅበር
9. ፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር
10. የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር
11. የወጣት ሴቶች ክርስቲያናዊ ማኅበር በኢትዮጵያ
12. የእራስ አገዝ ቡድኖች ህብረት /ይታወቅ ጥምረት/
13. እራስ አገዝ የሴቶች ድርጅት /ዋይዝ/
14. የሴቶች ማረፊያ እና ልማት ማኅበር
15. አዲስ አበባ ከተማ ሴቶች ማኅበር
16. የጋምቤላ ክልል ሴቶች ማኅበር
17. የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ሴቶች ማኅበር
18. አማራ ሴቶች ማኅበር
19. የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኛ ሴቶች ብሔራዊ ማኅበር
20. ቤዛ ውመንስ አሶሴሽ ኢን ኒድ
21. ቁመን የሴቶች ልማት ማኅበር
22. የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን
23. የኢትዮጵያ ወጣቶች ፌዴሬሽን
24. ኒው ሚሊኒየም ውመን ኢምፓወርመንት ኦርጋናይዜሽን
25. ጉድ ሳማሪታን አሶሴሽን
26. ምዥዥጓ ሎካ የሴቶች ልማት ማኅበር

# የኢትዮጵያ ሴቶች
# ሚኒፌስቶ
## ግንቦት 2013



**ኢ.ሴ.ማ.ቅ**

**በኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት**
**ቅንጅት የታተመ**